# እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20/2019 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊት እና የማለዳዉም ቅዝቃዜ በአንዳንድ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ እንደቀጠለ ተስተውሏል፡፡ የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀትም በተጠቀሱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ5 ዲግሪ ሴልሽያስ በታች ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎች ላይም ከዜሮ ዲ.ሴ. በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህል በጅማ -1.6፣ በመሃልሜዳ -1.8፣ በባቲ -1.5፣ በደብረብርሃን -1.2፣ በሀረማያ -0.8፣ በቢሾፈቱ -0.6፣ በጂግጂጋ 0.0፣ በወገልጤና 0.8፣ በባሌሮቤ 2.5፣ እና በማይጨዉ 4.2 በዲግሪ ሴልሽያስ ይገኙበታል፡፡

ባለፉት አሥር ቀናት የነበረው ዝናብ በመጠንና በዝናብ ቀናት አኳያ ሲገመገም በጎሬ 0.3 ሚ.ሜ. ዝናብ ለ1ቀናት ያህል ከተመዘገበው በስተቀር በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎ ሰንብቷል (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት አሥር ቀናት መላው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ከመቆየታቸው ጋር ተያይዞ በመላው የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ከመደበኛው በታች የሆነ ነበር (ካርታ 3) ።

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3    እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ
መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ የሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖባቸው እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከነበረው ደረቃማው እርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንከር ያለ ገፅታ እንደነበረው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ምንም እንኳን ደረቃማዉ የእርጥበት ሁኔታ የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ባላተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በጎ አስተዋፅዖ የነበረው ቢሆንም፤ የተስተዋለው የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተወሰነ መልኩ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎች፤ በጓሮ አትክልቶችና በእንስሳት ምርት ላይ አሉታዊ ጎን ነበረዉ (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2019 የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማና ፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል፡፡ የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ እንደ አለፈው አስር ቀናት በሁሉም ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ፀሃያማ ሁኔታ ነበር። ይህም ሁኔታ በሁሉም ተፋሰሶች እና በውሃ ሃብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሳደረ ቢሆንም፣ በሌላ በኩል የነበረው ቀዝቃዛ አየር የተፋሰሶችን ውሃ የትነት መጠን እንዲቀንስ በመጠኑም ቢሆን አውንታዊ አስተዋፆ ነበረው (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2019 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በሁሉም የአገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ እንደሚቆይና ከዚሁ ጋር ተያይዞም እንደቀደሙት ቀናት የተጠናከረ ባይሆንም፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩልም በመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ጥቂት ቀናት ውስጥ በጥቂት የመካከለኛው፣ የደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ የደመና መጨመር እንደሚስተዋል ይጠበቃል።

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የበጋው ደረቃማው እርጥበት ከፀሐያማና ነፋሻማ ሁኔታ ጋር ተዳምሮ በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የሚስተዋልበት ሲሆን፤ በተጨማሪም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃራዊ ሁኔታ ጋብ እያለ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

በተሰጠው የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ሙሉ ለሙሉ ላላጠናቀቁ አካባቢዎች በጎ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊኖር እንደሚችል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ እንደባለፉት የተወሰኑ ቀናት ጠንካራ እንደማይሆን ይጠበቃል፡፡ ይህ የመቀነስ አዝማሚያ ለተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ የጓሮ አትክልቶችና ለእንስሳት ልማት ተግባራት በጎ ሚና ቢኖረውም፤ ቅዝቃዜው በቀጣይነት በሚታይባቸው አካባቢዎች ግን አሉታዊ ጎን ሊኖረው ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ በአስሩ የመጨረሻዎቹ ቀናት አካባቢ የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት ለበልግ አምራች አካባቢዎች የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል አንፃርም ሆነ የቅድመ ማሳ ዝግጅት ለማከናወን አዎንታዊ አስተዋፅዖ የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ አስተዋፅዖ ያበረክታል፡፡

## እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በሁሉም የአገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ እንደሚቆይ የትንበያው ያመላክተናል፡፡ በመሆኑም በሁሉም ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ በመሆኑ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚኖረው የውሃ ሀብትን ለብክነት ከሚያጋልጡ ድርጊቶች ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ ስራዎችን መሰራት ተገቢ ነው፡፡ በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ጥቂት ቀናት ውስጥ በጥቂት የመካከለኛው፣ የደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ የደመና መጨመርና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህ መሰረት በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ የማለዳው ቅዝቃዜ መኖር የአማካኝ የቀኑ ሙቀት አነስተኛ እንዲሆን አስተዋፅዖ በማድረጉ ለውሃ አካላት ትነትን በመቀነስ በኩል በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡